# የወያኔን ባንዲራ ለሚለጥፉ ድረ-ገፆች ማሳሰቢያ

ከመዝገቡ ባየህ

ሁለት ወዶ አይሆንም ይላል ብልሁ የሀገራችን ሰው። የሀገር ፍቅርና የንዋይ ፍቅር በአብላጫው አብረው አይሄዱም። ጸረ ወያኔ ነን የሚሉ አንዳንድ ድረ-ገፆች የማስታወቂያ ገንዘብ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሲሉ የወያኔን ባንዲራ እፊት ለፊት ለጥፈዋል። አሰቡትም አላሰቡትም የወያኔን ከይሲ ባንዲራ የኢትዮጵያ ብለው እያቀረቡ ናቸው። ይህ ታዲያ ምን ይባላል? ገንዘብ ወዲህ መርህና አቋም ወዲያ? ታሪክና ቅርስ እንደ ምስጥ እየበላ ያለው ወያኔ የቀመመውን መርዝ መርጨት አይሆንምን?

አንዳንዶቹም ከዚሁ የጥንቆላ ምልክት ካለበት ባንዲራ ጋር ጨምረው ኢትዮጵያዊያን ሴት (Ethiopian Girls) ወጣቶችን እያማለሉ እራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ የሚያበረታቱ ድረ-ገፆችን ያስተዋውቃሉ። ከማን ጋር ነው እንዲተዋወቁ የምናደፋፍራቸው? ምን ያህልስ ሊያጋጥም ከሚችል አደጋ እንዲጠነቀቁ እንመክራቸዋለን? ብዙ ብዙ ሃላፊነትን የሚያጭሩ ጥያቄዎች የሚያስነሳ ነው ይኸ ጉዳይ። ኢቲቪን ተመልከቱ የሚል ማስታወቂያም የሚለጥፉ አሉ። እንደ አንድ የዜና ምንጭ የሚያስተዋውቁ። በዚህ በዚህ መልክ ለወያኔ እና ለሌሎች ጸረ-ኢትዮጵያ ፕሮፓጋንዳ መድረክ እየሰጡ፣ በተቃዋሚው ጎራ የቆምኩ ድረ-ገፅ ነኝ ማለት ፍዬል ወዲያ፣ ቅዝምዝም ወዲህ እንዲሉ ይመስለኛል።

የወያኔን ባንዲራ በማስታወቂያ ሽፋን በድረ-ገፃቸው የለጠፉ ሁሉ በአስቸኳይ እንዲያነሱ እነሆ ወገናዊ ማሳስቢያዬን አቀርባለሁ። የሀገርን ሰንደቅ ዓላማ አዋርዶ የሚመጣ ገንዘብ ወይም የደረጃ መሻሻል ይቅርብን ወገኖች -- ሀገራችንን እናስቀድም። ለይስሙላ ሳይሆን ተግባራዊ በሚሆን ጽኑ ሀገር ወዳድ አቋም።